# ሰብአዊና ዲሞክራሲ መብቶች

ይልማ ኃይለ ሚካኤል

June 18, 2018 -

*ሀ*

ፍሬ ከርሲኪ ያዘሉ መልእክቶችን በአገሪቱ እንደ ገደል ሜሚቶ ከሚለቁት ከቀስቃሾችና ከፕሮፓጋንዳ ካድሬዎች ጩኸት ሌላ በአለፉት አመታት ይህ ነው የሚባል ተጨባጭ መፍትሔዎች እና መልሶች በአገሪቱ ውስጥ አልታዩም፡፡ በየአለበት የምናየው ችግር ነው፡፡ ቀውስ ብቻ ነው፡፡ ችግር በየእንዳንዱ ቤት ውስጥ አለ፡፡ችግር በከተማይቱ ይታያል፡፡ችግር በገጠር፣ከዚያ አልፎም ችግር በመስጊዶችና በቤተ ክርሲቲያን ውስጥም ተስፋፍቶአል፡፡ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ደግሞ አሁን በድንገት ብቅ ያሉ አይደሉም፡፡ቆይቶአል፡፡ አሁን ባሰበት እንጂ!



አሥራ ሰባቱን አመት በተከታታይ — በደርግ የግዛት ዘመን- ሕዝቡን እንደ ጥላው ያጀበው ይኸው ችግር ነው ፡፡ አንድም መልስ ሳያገኝ በአለፉት ሃያ ሰባት አመታት ቀጥሎበት አሁን ያለበት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶአል፡፡ በአራቱም ማዕዘን -በገጠሩም ሆነ በከተማው- ፍጥነቱ ጨምሮ በየአለበት እየፈላ ነው፡፡ ሥራ ፈላጊውና ዳቦ ጠያቂው በሚሊዮን የሚቆጠር ነው፡፡ ጦሙን ውሎ ጦሙን የሚያደር ረሓብተኛ እንደዚሁ ብዙ ነው፡፡ እንደሚባለው መድሓኒት የለም፡፡ገንዘብም የለም፡፡የብርድ ልብስ የለም፡፡ መብራትና ወሃ እንደ ልብ አይገኝም፡፡ደሃው ማረፊያ ቤት የለውም፡፡የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ፈራስዋል፡፡ ለአስተማሪና ለመንግሥት ሠራተኛ ደመወዝ እስከ ምንጊዜ ድረስ እንደሚከፈል አይታወቅም፡፡

ችግሮቹ ሁሉ እንዴት ይፈታሉ! ቅድሚያ በመጀመሪያ ለይተኛው ይሰጠው!....ለመሆኑ ሌሎች ሕዝቦች፣መንግሥታት ፣አውሮፓያኖችስ፣ ለችግሮቻቸው ከሞላ ጎደል እንዴት እነሱ መልስ አገኙ!

ለምንድነው እነሱ ሰላም አግኝተው ሥራቸውን እየሠሩ ወደ ላይ የመጠቁት! እኛስ ለምንድነው እርስ በእራሳችን በሆኑ በአልሆኑ ነገሮች ጥዋት ማታ ለአለፉት ሃምሣ አመታት የምንደናቆረው!...ይህን ረጋ ብሎ መመልከቱ ጥሩ ነው፡፡

አንድ ሌላ ትልቅ ችግር ደግሞ በአገሪቱ በኢትዮጵያ ውስጥ አለ፡፡እሱም እንደ አክሱም ሓውልት ለአለፉት ብዙ መቶ አመታት በመካከላችን ቀጥ ብሎ የቆመ ችግር ነው፡፡ ማንም ማየት የሚፈልግ ሰው በቀላሉ የሚያየው ችግር ነው፡፡ እሱም ሰው ሁሉ ይህን ጉዳይ አንስቶ፣ በዚያ ላይ ለመነጋገር የሚፈራው ችግር ነው፡፡እንደምናውቀው የቅስቀሳወና ፕሮፓጋንዳው ክፍል በየጊዜው አንስቶ እንደ ትልቅ ቁም ነገር የሚያነሳቸው ነገሮች አሉ፡፡ እነሱ ግን በምንም ዓይነት ከተጨባጩ የአገሪቱ ሁኔታዎች ጋር ግንኙነት የላቸውም፡፡

„....ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ እባክህን ይህን አድርግ ! ያን ፍጠር ...„ የሚሉ ከሁሉም አቅጣጫ የሚወጡ የጥር ደብዳቤዎችን በአሁኑ ሰዓት እናነባለን፡፡የተለያዩ መላምቶችንም እንደዚሁ ከሌሎቹ እንሰማለን፡፡ነገሩ ጥሩ ነው፡፡ ግን ስለ አንድ ነገር አፍርጠን እስከ አልተነጋገርን ድረስ ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያዊነቱዋ ልትኖር አትችልም ፡፡ የማነሳው በአለፈው ጊዜ „ይቀጥላል "ብዬ ስለ አሳደርኩት ዋስትና ስለሚሰጠን ፣ስለ ዲሞክረሲ መብቶች፡- ስለ የመናገር ነጻነት ነው!

አሱን ያኔ በዘመኑ ጨብጥን ቢሆን ኑሮ እነ ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሓብተውልድን፣እንደገና ሁለቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮችን እነ እንዳልካቸው መኮንን እና እነ ልጅ ሚካኤል እምሩን — ከሌሎቹ ትላልቅ የአገሪቱ ሊህቃን ጋር አባረው- " ለመቅደዱ" የሞከሩቱን ሜዳ ፤ደርጎቹ፣ ለእነ ኮነሬል መንግሥቱ ኃይለማሪያም „..ነግሠው" እንዲጨፍሩበት ለእነሱ ባልተለቀቀ ነበር፡፡

„የፓርላማ ሥርዓት፣....የፕረሴ ነጻነት" እነሱ ከአገሪቱ ጋር ለማስተዋወቅ ጥረት አድርገው ነበር፡፡ በተለይ „የፕሬስ ነጻነቱ"

ዘመን አይረሳም፡፡ „እንደ ትኩስ ዳቦ" ሰው ሁሉ የአገሪቱን ጋዜጣዎች ተሻምቶ ይገዛ የነበረበት ዘመን ነበር፡፡

ደርግንም ሌሎቹ ተከተው ለአለፉት 27 አመታት ብቻቸውን በአልገዙም ነበር፡፡

የአገር ችግር፣ያውም የተወሳሰበውን የኢትዮጵያን ችግር እንኳን አንድ ሰው፣እንኳን አንድ ቡደን „ፊደል የቆጠረው ክፍል" ሁሉ ተሰባስቦ ብቻውን የሚፈታው ነገር አይደለም፡፡ መፍትሔዎች የሚገኙት እታች ወረድ ብላችሁ በምታዩአቸው አንዳንድ አስተያየቶች ነው፡፡ ….በክርክርና በውይይት፣በምርመራና በጥናት፣በመደማመጥና በመቻቻል ነው! ይህ ደግሞ እራሱን የቻለ „የጨዋታ ሕግጋት" አለው፡፡ይህ ደግሞ ወረድ ብላችሁ እንደምታዩት መሠረታዊና ማንም የማይሽረው የሰው ልጆች መብት፣መብቶች ሲከበሩ ብቻ ነው፡፡

መልካም ንባብ!

ለ

ሰብአዊና ዲሞክራሲ መብቶች

እንደዚህቹ ጽንሰ-ሓሳብ – ማራኪ ስለሆነች – እጅግ አድርጎ ልብን የሚማርክ፣አእምሮን የሚስብ ቃል የለም፡፡የዚያኑ ያህል ደግሞ እንደዚህች ቃል ሰውን ሁሉ የሚያከራክር፣ ግራም የሚያጋባ፣አልፎ ተርፎም – ከአልታወቀበት እና በጥንቃቄ ከአልተያዘ- ወደ አንድ ወደ የማይታወቅ „ሥርዓት" ሰውን ሁሉ ነድቶ የሚወስድ ቃል የለም፡፡

ሁሉም ሰው ቢጠየቅ መልሱ „እኔ ዲሞክራት"ነኝ ባይ ነው፡፡ ሊበራሉም፣ኮንሰርቨቲቩም…ከዚሁ ጎራ ናቸው፡፡ሶሻል ዲሞክራቱም፣መሓል ሠፋሪውም፣ አርበኛውም፣አገርወዳዱም እነዚህ ሁሉ „ዲሞክራት" ናቸው፡፡ ነጻ-አውጪው፣ ድልድይ አፍራሹም፣ባንክ ዘራፊውም፣ የደፈጣ ተዋጊውም – ሁሉም ቢጠየቁም- መልሳቸው„…ዲሞክራት" ነው፡፡ አክራሪ እስላሙም ፣አንገት ቆራጩ ሽፍታ፣ ሠልፉን አሳምሮ እራሱን የሚመድበው ከእነዚሁ „ከዲሞክራቶቹ" ጋር ነው፡፡ ኮሙኒስቱም፣ፋሽሽቱም – ቀደም ሲል እነሱ ስለ ራሳቸው እንደጻፉት- አለማወላወል ሲጠየቁ፣እነሱም በመልሳቸው፣እንከን የማይወጣላቸው„… ዲሞክራት „ ናቸው!

ዲሞክራሲን ሰዎች እንዴት እንደሚተረጉሙት፣ እነሱም እንዴት ይህን ቃልና ሥርዓት፣ እንደሚያዩት የቅርቡ የአርባ፣ወይም የሃምሣ አመት ታሪካችን ጥሩ ምስክር ነው፡፡ይህ ደግሞ መለስ ብለን ከአየነው ትምህርት ይሰጣል፡፡ ግሩም ምሳሌ ነው፡፡

በጀርመን አገር እና በጣሊያን ሁለት ፋሽሽት ድርጅቶች የዲሞክራሲ ሥርዓቱ የሰጣቸውን „መብት" ተጠቅመው „በሕዝብ" ተመርጠው ሥልጣን ላይ እነሱ ወጥተዋል፡፡ወጥተው የሚታወቀውን በዝርዝር ለአለመድገም ወንጀል ሠርተዋል፡፡ በሩሲያ እና በቻይና እንደዚሁ ኮሚኒስቶቹ -የተረሳውን ለማስታወስ- የዲሞክራሲን ጥያቄ አንስተው „..የላብ አደሩና የገበሬው አምባገነን መንግሥት" በሕዝቦቻቸው ላይ ዘርግተዋል፡፡ ሓሳቡም ተስፋፍቶ ከምሥራቅ በርሊን እስከ ዋርሶ፣ከሶፊያ እስከ ሄኖይ፣ ሰሜን ኮሪያና ካምቦጂያ፣ከሓቫና እስከ አሥመራ፣አዲስ አበባና ሓራሬ ድረስ „በዲምክራሲና በዲሞክራቶች ስም" ትልቅ መረብ ተዘርግቶአል፡፡ አንድ ሦስተኛው የዓለም ካርታ እነሱን በቀይ ቀለም ያሳይ ነበር፡፡ ግን በእሥራት ያለቁትን፣የጥይት የተደበደቡትን ታሪክ የሚያውቅ ቁጥሩ „ትንሽ" ነው!

ማንም ሰው የፈለገውን ትርጉም „ለዲሞክራሲ" ሰጥቶ እንደ ኳስ ወደ ፈለገበት አቅጣጫ የሚለጋትም ነገር ከሆነች ደግሞ ጊዜው ረጅም ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ ጥልቅ ዕውቀት አላቸው ተብሎ የሚነገርላቸው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ እንኳን በአዲስ አበባው ጉብኝታቸው ላይ ለዚህ ጽንሰ-ሓሳብ አዲስ ትርጉም ሰጥተው አንዳንዶቹን አስደስተዋል፡፡ብዙዎቹንም ፕሬዚዳንቱ – ለማስታወስ- አስቀይመዋል፡፡ይህ ግን አይረሳም!
ጽንሰ ሓሳቡ ለአንዱ „…ክብሩ" ነው፡፡ ለሌላው መግቢያውና የመጠለያ ቤቱ ነው፡፡ማንም የማይገፈውና ማንም በጫማው የማይረግጠው ከእግዚአብሔር በተፈጥሮው የተሰጠው መብቱ ነው፡፡ ስለሆነም የሰው ልጆች ሁሉ ይኮሩበታል፡፡በተፈጥሮ ለአንተ እና ለእኔ፣ ለአንቺኛ ለእሱ፣ ለሰው ልጆች ሁሉ እኩል ከአምለክ ያገኙት የተሰጠ፣የማይሸጥ የማይለወጥ መብታችን ነው፡፡ ይህን የሚያውቁ ብዙ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ዲሞክራሲ – በአንዳዶቹ እምነት – ለምዕራቡ ዓለም ለነጮቹ ብቻ የተሰጠ „ ልዩ መብት" አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ይህንንም በአደባባይ የሚያስተምሩ፣መጽሓፍ ጽፈው የሚሸጡም ሰዎች አሉ፡፡ እንደ ሰይጣን ደግሞ„… የዲሞክራሲ ጠበሉ" እንዳይነካቸቸውና እንዳያረጥባቸው „…የሚሸሹም" ሰዎች ቁጥር በአፍሪካም ሆነ በመካከለኛው ምሥራቅ ትንሽ አይደሉም፡፡

ዲሞክራሲ„እኩልነትና ሥልጣንን ማጋራት" ስለሆነችም ይህቹን ቃል ፈጽሞ እንዳትነሳ „በሕግ የሚከለክሉ" መንግሥታትና ኃይሎች አሉ፡፡

„ሙብቴ" ከአልተጠበቀ ምን አደርጋለሁ ብሎ አገሩን ጥሎ የሚሰደድ ሰው ሞልቶአል፡- በሚሊዮን ይቆጠራሉ፡፡„ሙብቴ " ይከበር ስለአለ ብቻ እሥር ቤት የሚወረወሩ አሉ ፡፡ ደፍረው ይህን ጥያቄ በማንሳታቸውም፣ የሚገርፉ፣የሚሰቀሉ፣በጥይትም የሚደበደቡም አሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ የተሰበሰበ በቂ ማሥረጃ በዓለም ላይ አለ!

"…..አርፈህ ተቀመጥ ጊዜው አይደለም!" የሚሉም መካሪም፣ተቆጪችም ትንሽ አይደሉም፡፡ እንዲያውም ከእነ አካቴው„… ለእናንተ ለጥቁር አፍሪካውያኖች ዲሞክራሲ አይጠቅማችሁም"ብለው የሚዋሹ ነጮች ብዙ ነው፡፡„ለአንድ ሰው አንድ ድምጽ" የሚለው የዲሞክራሲ መመሪያ „በኢትዮጵያ ውስጥ አይሠራም.." ባዮቹ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ትንሽ አይደሉም፡፡

ለመሆኑ „ዲሞክራሲ" የሚባለው ሥርዓት እና የአኗኗር ዘይቤ ከየት መጣ! …እንዴትስ ተጀመረ! …ከዲሞክራሲ በፊት ምን ዓይነት ሥርዓት ነበር!…የት ቦታ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ይህ ቃል የተሰማው! …ዲሞክረሲ ለማን!… ዲሞክራሲ ለምን! … ዲሞክራሲ በገደብ ፣…. ዲሞክራሲ አለገደብ! ለመሆኑ ነጻነት ምንድነው፣…ነጻነት ለማን፣…. ነጻነት ለምን!….ለእነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ቀደም ሲል የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪዎች በቂ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

ግን ያም ቢሆን አሁንም ድረስ ትውልዱን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያከራክር አርዕስት ቢኖር ይህ „….ዲሞክራሲ" የሚባለው ነገር ነው፡፡ በአልሆነ ቦታ ፣ከአልሆነ ሰው ጋር ይህን አርዕስት አንስቶ የሚከራከር ሰው ጥይትንም „ሊቀበል" ሰቆቃም ሊወርድበት ይችላል፡፡ ስለዚህ ጠንቀቅ ማለትን ይጠይቃል፡፡

ወሬ ሳይሆን፣ እኔ አሁን እንደገና አንስቼ ለመመልከት የፈለኩት „ዲሞክራሲ" በዓይን የሚታይ፣ በእጅ የሚዳሰስ ሥርዓት ነው፡፡ በቀላል ቋንቋ ነገሩን ለማስረዳት ሐኪሙ „ልጅቱዋን „መርምሮ በመጨረሻው የሚሰጠው ፍርድ ዓይነት ነው፡፡ ልጅቱዋ„…አረግዛለች ወይም አላረገዘችም" እንደሚለው ዓይነት ነው፡፡

የሚታወቀውን ለመድገም ፣ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ „…ግማሽ እርግዝና" እንደሌለ ሁሉ „..ግማሽ ዲሞክራሲም" የሚባል ነገር በዚህች ዓለም ላይ የለም፡፡በአጭሩ ዲሞክራሲ በአንድ አገር አለ ወይም የለም ለሚለው ጥያቄ የምናገኘው መልስ ወሳኝ ነው፡፡

ግን ይህ የገ!ዳ! ሥርዓት የሚባለው ነገር ምንድነው! ከየትስ መጣ! ለመሆኑ ይህ „ሥርዓት" ማንን ይጠቅማል!!

ያ አሁን እንደገና ከሠላሣ አመት በኋላ፣ እንደ አዲስ ነገር ብዙ የሚነገርለት „አብዮታዊ ዲሞክራሲ „ ፍልስፍና ለመሆኑ እሱ ምንድነው! „…ልማታዊ ዲሞክራሲስ" ምን ማለት ነው!

ሐ

የሰው ልጆች ሁሉ ሕልምም ራዕያም አላቸው…

ስለ „…ነጻነት፣ስለ ሰበአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች፣ስለ ሰበአዊ ክብር.." ለመጻፍና ለማስረዳት- ከቡራትና ከቡራን- በየትኛው አቀራረብ ልጀምር የሚለው ነገር ብዙ ጊዜዬን ወስዶብኛል፡፡

ከሕግ አንጻር ልጀምር ወይስ ከሕብረተሰብ ሳይንስ፣…ከሰው ልጆች ታሪክ ወይስ ከፍልስፍና መጻሕፍት፣ከተፈጥሮ ሳይንስ፣ ከባዮሎጂ ወይስ ከሃይማኖት ትምህርቶች፣ነብዮችና ሐዋሪያት ከጻፉት መልዕክቶች ፣ወይስ ከአይዶሎጂ ወይስ ደግሞ ከፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ፣ከመሪዎቻቸው ጽሑፍ ፣ ከአውሮፓ ሥልጣኔ፡- ከእላይትመንት፣ከብርሃን ዘመን ወይስ ከሥነ-ልቦና ትምህርት፣ከልብ ወለድ ድርሰቶች ወይስ እንደ ማርቲን ሉተር ኪንግ „ አንድ ሕልም አለኝ" ከሚለው ንግግሩ፣ከየትኛው ልጀምር የሚለው ጥያቄ ጭንቅላቴን አዙሮት ነበር፡፡ የምዕራቡንና የምሥራቁን ሥርዓት በማወዳደር ልጀምር ወይ ብዬ እራሴን ጠይቄ ነበር! ግን ትልቅ ድረሰት ለመጻፍ አሁን ጊዜው ስለ አልሆነ ተውኩት፡፡

ሕልም ጥሩ ነው፡፡ራዕይም መልካም ነው፡፡ ግን ከሕልም ሲነቁ ደግሞ በዓይን የሚታየው ተጨባጩ ነገር… አንዳንዴ የማይቀመስም የማይላስም፣…. እሬት፣እሬት የሚልም ሊሆንም ይችላል፡፡

ይህ እንዳይሆን ለመሆኑ ምን ዓይነት ዋስትና፣ምንስ የሚባል „ጋራንቲ" በእጃችን ላይ – በኢትዮጵያ አሁን አለ፡፡ ለመሆኑ እንደ ራስ ተፈሪና እንደ ልጅ ኢያሱ „የሰገሌ ጦርነት" ውስጥ ተመልሰን እኛ እንዳንገባ ምን የሚያግደን ነገር አለ! ምንስ ዓይነት የመከላከያ ጋሻ በእጃችን ጨብጠናል፡፡„የባድሜ" ዓይነቱ ጦርነት በአገሪቱ ተመልሶ እንዳይገረሽ የምንከላከልበት – የዲሞክራሲ መሣሪያችን – ምንድነው !

እንደ ሁለቱ የሚተዋወቁና የሚግባቡ „ጓደኞች" እንደ ኮነሬል መንግሥቱ ኃይለማሪያምና እንደ ኮኔሬል አጥናፉ አንድ ቀን ሰዎች በአገራችን ተነስተው ሊተናነቁ፣ሊገዳደሉ ይችላሉ፡፡ሁለቱ ወይም ሦስቱም „የአገሪቱ መሪዎች" በመካከላቸው ጦርነት

እንዳይከፍቱ እነሱን የሚያግዳቸው ነገር ምንድነው! እንደ መለሰና እንደ እነ ሰዬ አብረሃ ፤…እንደ አነግና እንደ ወያኔ፣…እንደ መኢሶና እንደ ኢህአፓ፣አሁን በአገሪቱ ውስጥ የምናያቸው  ድርጅቶች „የእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ" ዛሬ ባይሆን ነገ ፣ ወይም ከነገ ወዲያ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ከገቡስ! ምን ይመጣል! እንዳይገቡስ የሚግዳቸው የተዘረጋ ሜካኒዝም ምንድነው!

ለመሆኑ አገሪቱ ኢትዮጵያ ከአንድ ቡድን አምባገነን ሥርዓት ተላቃ እንዴት አድርጋ ነው ወደ ዲሞክራቲክ ሥርዓት የምታመራው! ልታመራስ ትችላለች ወይ! ምንድነው እንደ „ድርና ማግ" እንዳንበታተን፣እንዳንፈረካከስ አሥተሳስሮ የሚይዘን ነገር!

ይህን ሁሉ ጥያቄ ለእራሴ አንስቼ ሳስብበት- ክብራትና ክቡራን አንባቢዎቼ-  አንዲት ብጣሽ ነገር በሳምንቱ መጨረሻ ላይ እጄ ላይ ወደቀች፡፡ እሱም አንድ አሽሟጣጭና ቀልደኛ ሰዓሊ ለአንድ ለታወቀ ሳምንታዊ መጽሔት „የሞነጫጨራት" ካርቱን ሥዕል ናት፡፡ ይህቺን ሓሳቡን ይህ ሠዓሊ በመካከለኛው ክፍለ-ዘመን ወረቀት ላይ አሥፍሮ ቢበትናት ኑሮ፣ ያኔ እነሱ እንደሚቀጡት የፈጢኝ፣ እጅና እግሩን አንድ ግንድ ላይ አሥረው፣ችቦ ከምረው እሳት ይለኩሱበት ነበር፡፡

ምን እዚያ አስኬደን፡፡ በቅርቡ በፓሪስ ፣ቀደም ሲል በዴንማርክ „በሃይማኖት" ላይ ቀለዳችሁ ተብለው በአክራሪዎች ጥይት ብዙ ጋዜጠኞች ተደብድበው ሕይወታቸወን አጥተዋል፡፡

ሥዕሉ ይህን ይመስላል፡፡

አንድ ዕድሜው በጣም የገፋ የነጣ ረጅም ጢም ያለው አዛውንት ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፣ አንድ ጋዜጣ በሁለት እጁ ይዞ እሱን እያገላብጠ፣ ተገርሞ ዜናውን ይከታተላል፡፡ከዙፋኑ ግራ እና ቀኝ በአዛውኑቱም እግሩ ሥር  ደመና እና ጉም ይታያል፡፡በገና ይዞ አንድ መላአክ ፣ ራቅ ብሎ  ክንፉን ዘርግቶ የምሥጋና ዝማሬውን ያደርሳል፡፡ ከዘፋኑ የጀርባ መደገፊያው ላይ በሦስት ማዕዘን ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አይን ይታያል፡፡ ተገርሞም ይኸው አዛውንት አንድ ነገር ይናገራል፡፡ „..ይህ ፑቲን የሚባል ሰው ምን ዓይነት ታምራተኛ ልጅ ነው እባካችሁ!….ጠላቶቹን ጥግ አስይዞ መጨረስ ብቻ ሳይሆን፣የገደላቸውንም ሰዎች ከሙታን ዓለምም፣ከከርሰ-መቃብሩ እንደገና እነሱን ማስነሳት ለካስ ይችልበታል!" የሚለውን ቃል ሠዓሊው ለጥፎበታል፡፡

እንደዚህ ዓይነቱን  ሓሳብ ወረቀት ላይ አስቀምጦ በመካከለኛው ክፍለ-ዘመን ማሰራጨት አለጥርጥር ሠዓሊውን ያስቀጣው ነበር፡፡ ሥዕሉም ፣ጋዜጣውም፣እዚያም ዩኪሬን ውስጥ ያ የሩሲያ ጋዜጠኛ እና የአገሪቱ የጸጥታ ፖሊሶች አንድ ላይ ተመካክረው እዚያ የአደረጉት ሥራ… ነው፡፡ አሁን በያዝነው በ 21 ኛ ክፍለ-ዘመን በመሆኑ እንጂ እነሱንም የሚያስቀጣ ፣ከአልሆነም የሚያስከስስ ሥራ ነው፡፡

ጉዳዩ- እንደምታውቁት ብዙዎቹን የሚያነጋግር አርዕስት ሁኖአል፡፡ „ይህን ማድረግ ተገቢ ነው! ወይስ አይደለም" የሚለውንም ጥያቄ ብዙ ቦታዎች አስነስቶአል፡፡ „ …ጋዜጠኞች እና የጸጥታ ሰዎች አብረው መሥራት አለባቸው ወይ!…እስከ ምንስ ድረስ ነው „ፈጠራና" እውነተኛ ታሪኮች  ጎን ለጎን አብረው የሚሄዱት!" የሚለውን ተጨማሪ ጥያቄም እዚህ እንደገና አስነስቶአል፡፡ „…እግዚአብሔርስ ሥራ ፈቶ ዕለታዊ ጋዜጣዎችን ፣ከመቼ ወዲህ ነው የሚያነበው!" የሚሉም ተነስተዋል፡፡

መ

የሰውን ልጆች „አሥሮ ፣በምርመራ አሰቃይቶ በእሳት ማቃጠል" የተከለከለው ከብዙ መቶ አመት በፊት ነው፡፡ እንደሚታውቀው የካቶሊክ ቤተ-ክርሲቲያን በመካከለኛው ክፍለ-ዘመን ይህን የምርመራ ዘዴ ተጠቅሞ ብዙ አማኞቹን „ሰይጣን ይዞአቸዋል" ብሎ እሳት ያነድባቸው ነበር፡፡ ጸሓፊው ኡምበርቶ ኤኮ „ጽጌረዳ" በሚለው ድርሰቱ ይህን ሁኔታ ጥሩ አድርጎ ለአንባቢዎቹ አቅርቦአል፡፡ በሕግ ከዓለም ላይ እንደዚህ ዓይነቱ ነገር በሰው ልጆች ላይ እንዳይፈጸም በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ተከልክሎአል፡፡

ከእሱም ጋር አንድ ሰውን ባሪያ አድርጎ መግዛትና መሸጥ፣እቤቱም ውስጥ አሥሮ መብቱን ገፎ እንደ አህያ እየገረፉት ማሰራት በሕግ የተከለከለው በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ነው፡፡ በመጀመሪያ በአሜሪካን በኋላ በብራዚል፡፡

ሕጎቹ  በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ  ኢትዮጵያ  ደርሰው አጼ ምኒልክ „ አንድ ነፍስ ያጠፋን ሰው ፣ሰውዬውን እሱ እንደገደለው ዘመዶቹ ፣በተራቸው ቆራርጠው እንዳይገድሉት" ከባሪያ ንግድ ጋር በሕግ ክልክል መሆኑን በአዋጅ አግደዋል፡፡ይህም „ስለ ሰበአዊ መብት እና ሰበአዊ ክብር በአፍሪካ እና በኢትዮጵያ" ስናወራ የማይናቅ ትልቅ እርምጃ ነው፡፡

ስለ „…ሰበአዊ መብት ማውራትና መናገር መቼ ተጀመረ…" ! ለሚለው ጥያቄ ከተለያዩ የትምህርት ዘርፎች የበቀሉ፣ ብዙ ተመራማሪዎች፣እንደ የሙያ ዝንባሌዎቻቸው፣ከተለያዩ ቦታዎችና ምንጮች ዕውቀታቸውን ቀድተውና ሰብስበው ለእኛ

ያከፍላሉ፡፡

ከ 1948 የሚጀምሩ አሉ፡፡ 1975 ዓ.ም.እ.አ.አ. የሚጠቅሱም አሉ፡፡ከመንፈሳዊ ኮሌጆችና ከተለያዩ የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች ተመርቀው የወጡት ደግሞ የሓዋሪያት ሥራን፣ የክርስቶስ ትምህርት እያገለባጡ -የሰው ልጆች መብት ጉዳይ ከሁለት ሺህ አመት በፊት አርዕስት ሁኖ እንደተነሳ እና በዓለም ዙሪያ እንደተሰራጨ ፣ማሥረጃቸውን ያቀርባሉ፡፡ እዚሁ ላይ እነሱ ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳንን፣የፕላጦስ እና የአርስጦፐለስ ጽሑፎችና ትምህርትን ይጠቅሳሉ፡፡ ሌሎቹ የሩሲያንና የቻይናን አብዮት ሳይሆን -እነሱ ስለ ሰበአዊ መብቶች መከበር ምንም ያበረከቱት አስተዋጽኦ የለም- የአሜሪካንና የፈንሣይ አብዮት አዋጆችን እንደ መሠረት ድንጋይና እንደ ምሶሶ ያነሳሉ፡፡

አንድ በቅርቡ እጄ ላይ የወደቀው ጥናት ደግሞ „ቅዱሱ ሰው‟ በሚለው አርዕስቱ እኛ ከምናውቃቸው ከትላልቅ ሃይማኖቶች በፊት- ማለት ከዛሬ አሥር ሺህ አመት በፊት- በሕንድም ፣በቻይናም፣በግሪክም፣በመካከለኛው ምሥራቅ እና በአፍሪካ- „የሰው ልጆች ሁሉ በእኩል ዓይን የሚተያዩ ፣የሰማይ ልጆችና ወንድማማቾች…ናቸው‟ ብለው ዱሮ ያምኑ ነበር ብሎ ያስተምራል፡፡ በአጭሩ „ የሰው ልጆች ሁሉም እኩል አይደሉም‟ የሚለው አመለካከት በኋላ ዘግይቶ በተንኮለኞች እንደ ተነደፈ ይኸው ጥናት ይዘረዝራል፡፡

…አንድ ሕልም አለኝ‟ ይህ ሕልም-ብዙ ጊዜ እንደሚባለው- የማርቲን ሉተር ኪንግ ሕልም ብቻ አይደለም፡ — የሰው ልጆች ሁሉ ሕልም ነው፡፡ ሕልሙም ነጻነት ነው፡፡ እኩልነት ነው፡፡ ያም ምኞት የእያንዳንዱ ሰው ሰበአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ መከበር ነው ፡፡….አስተያየትን አመለካከቶችን በነጻ-ጋዜጣ ላይ አሥፍሮ ሌሎቹ እንዲካፈሉት ማድረግ ነው፡፡ …መሰብሰብ፣መደራጀት፣መናገርና ሓሳብን ማራመድ፣ ተንቀሳቅሶ መነገድ እና ማትረፍ ፣ ሐብትም ማፍራት እና ለልጆችም ማውረስ፣እነዚህ ሁሉ የሕልሙ አንደኛው ክፍል ናቸው፡፡ ይህ ሕልም ሌሎች ነገሮችንም ይጨምራል፡፡

ቃል በቃል ባርነትን ይቃወማል፡፡ግርፋትና ሰቆቃ፣በደል እንዳይኖር ይከላከላል፡፡ የአንድን ሰው ወይም የአንድ ቡድንን ፈላጭ ቆራጭነት ይጻረራል፡፡ ይህ ሌላኛው ክፍል ነው፡፡ ማንም ሰው የፈለገውን ሃይማኖትና እምነት መከተል ይችላል ይላል፡፡

አንዳንዶቹ ነጥቦች የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ላይ በደንብ ተገቢ ቦታቸውን ይዘው ተቀምጠዋል፡፡ሌሎቹ ደግሞ በማወቅም ይሁን በአለማወቅም ተዘለው ታልፈዋል፡፡

በአለፉት አመታት ብዙውን ጊዜ እና ትልቅ ቦታ በአገሪቱ የያዘው ጥያቄ በልዩነት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ „ …አብሮ እና ተቻችሎ ፣ተፋቅሮና ተግባብቶ በሰላማዊ ሁኔታ ውስጥ መኖርን ለሚያስተምረው ለዲሞክራሲ ሥርዓት‟ ቅድሚያ አልተሰጠውም ነበር፡፡ „…ዳቦም ሆነ ሥራን፣ ላላመጣው፣ ዕውቀትንም ሆነ ብልጽግናን ለላአስፋፋው..‟ እውነቱን እንናገር ከተባለ „ ዕድገትንም ሆነ ሥልጣኔንም ለአገሪቱ ለአላመጣውና ሊያመጣም ስለ አልቻለው‟ አንድ ነገር ብዙ ቦታ ተሰጥቶት በዚያ ዙሪያ ሰው ሁሉ ሲሽከረከር ወርቅማ ጊዜውን „አጥፍቶአል‟፡፡ ለምን!

እስቲ ብቻ በጀመርነው አርዕስት እንቀጥል!

ዲሞክራሲ „የብዙሃኑ ሕዝብ‟ መንግሥት ነው ሲባል ብዙ ጊዜ ሰምንተናል፡፡በዚህኛው አመለካከት እና ትርጉም ላይ፣ዱሮም ቢሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ሙሉ ስምምነት አለ፡፡ በዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ደግሞ — ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ እንደሚባለው- „የሥልጣኑ ባለቤት ሰፊው ሕዝብ‟ ነው፡፡ በዚህም አቀራረብ ላይ ልዩነት ፈጽሞ አይታይም፡፡ ሁሉም- ይስማማሉ፡፡ እንግዲህ በሌላ አነጋገር በእንደዚህ ዓይነቱ አቀራረብና አመለካከት „… እኔ እና አንቺ፣…አንተና እሱዋ፣…እሱና አንተ፣….ሁላችንም…የአገሪቱ ሕዝብ በሙሉ — በግልጽ ቋንቋ ለመናገር — „…የሥልጣኑ ባለቤት‟ ነን፡፡ እስከዚህም ቦታ ድረስ በትውልዱ መካከል — እኔ እንደአየሁት፣እኔ እንደ አዳመጥኩት- የጋራ ስምምነት አለ፡፡

ግን ደግሞ ከራሳችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ እንደምናውቀው፣ አለመግባባትና ረብሻው የሚነሳው — ለዚህ ብዙ ማሥረጃዎችና ምስክሮች አሉ — አንዳንድ ሰዎች የላይኛው አነጋገር መሠረት አድርገው „ …ዲሞክራሲ ማለት የብዙሃኑ ፣ የሰፊው ሕዝብ መንግሥት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የብዙሃኑ መንግሥት‟ — እነሱ እንደሚሉት- „በኣናሳው‟ እና ደግመው እነሱ አጥብቀውእንደሚሉት „ …በሌሎቹ በበዝባዦቹ፣ በከበርቴዎቹ፣ወይም በአንዱ በቀድሞ ገዢ ጎሣ ላይ የጭቆናውን ክንዱን ፣ያለማያወላውል አምባገነንነቱን ‟ በእነሱ ላይ „…አለርህራሄ ማሣረፍ አለበት‟ ሲሉ „ድብልቅልቁ‟ ይወጣል፡፡

ይቀጥላል፣ይቀጥላል….

ይልማ ኃይለ ሚካኤል

በርሊን 2018